እነዚህ ደንቦች፣ የሰራተኞቹ የኢምግሬሽን ሁኔታ ወይም አሰሪው የሚገኝበት ቦታ ሳይገድበውሁሉንም በሲያትል ከተማ ወሰን ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን ይሸፍናል።
አሰሪዎች በነዚህ ህጎች ይገዛሉ። የቂም በቀል እርምጃ ሕገወጥ ነው።

# 2024 የሲያትል ሰራተኛ መስፈርቶች ደንቦች

የሰራተኛ መስፈርቶች ቢሮ ተልእኮ፣ የሰራተኛ መስፈርቶችን በታቀደ የማህበረሰብ እና የቢዝነስ ተሳትፎ፣ ስልታዊ አፈጻጸም እና ፈጠራ የታከለበት የፖሊሲ እድገት ከዘርና ማህበራዊ ፍትህ ቁርጠኝነት ጋር ማሳደግ ነው።

ይህ ፓስተር በስራ ቦታ ላይ በሚታይ ስፍራ በእንግሊዘኛ እና ሰራተኞች በሚናገሩት ቋንቋ መለጠፍ አለበት።

የሰራተኛ መስፈርቶች ቢሮ ለአካል ጉዳተኞች ትርጉም እና ማረፍያ ይሰጣል።

## ዝቅተኛ ደሞዝ

ለሰራተኞች ዝቅተኛ ደሞዝ ይወስናል

### ትልቅ አሰሪዎች

(501 ወይም ከዚያ በላይ ሰራተኞች)

**$19.97**
በሰአት

### ትንሽ አሰሪዎች

(500 ወይም ከዚያ በታች ሠራተኞች)

አሰሪው ለሰራተኛው የህክምና ጥቅማጥቅም ቢያንስ በሰአት $2.72 ይከፍላል እና/ወይም ሰራተኛው ቢያንስ በሰአት $2.72 ጉርሻ ያገኛል?

| አይ | አዎ |
|---|---|
| **$19.97** በሰአት | **$17.25** በሰአት |

**የአሰሪው መጠን**
አሰሪው በአለም ዙርያ ያለውን የሰራተኞች ብዛት መቁጠር። ልዩ ፍቃድ ላላቸው፣ በዚያ ልዩ ፍቃድ ባላቸው አውታረ መረብ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሰራተኞች መቁጠር።

**የህክምና ጥቅማጥቅሞች— አነስተኛ አሰሪዎች**
አነስተኛውን የሰዐት ክፍያ መጠን ለመክፈል፣ በፌደራል **Affordable Care Act** (ተመጣጣኝ የህክምና ህግ) በተደነገገው መሰረት የአነስተኛ አሰሪ ክፍያዎች በብር-ደረጃ (silver) ደረጃ ወይም ከዛ በላይ የህክምና ኢንሹራንስ እቅድ መሆን ይኖርበታል።

» አነስተኛ አሰሪ ሰራተኛው ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ለህክምና ኢንሹራንስ ብቁ ካልሆነ አነስተኛውን መጠን መክፈል አይችልም።

## ከክፍያ ጋር የህመም እና የደህንነት ግዜ

ለህክምናና ከደህንነት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የሚከፈል እረፍት ይፈለጋል።

አሰሪዎች ሰራተኞቻቸው እራሳቸውን ወይንም የቤተሰብ አባላቸውን ለመንከባከብ ከክፍያ ጋር እረፍት ሊሰጥዋቸው ይገባል።
(ልጅ ፡ወላጅ፡ ባለቤት፡ የተመዘገበ የቤት ውስጥ አጋር፡ አያት ፡የልጅ ልጅ ፡ወንድም/እህት)

**የህመም ጊዜ፣** አካላዊ ወይም የአእምሮ ጤና ሁኔታ ፡የህክምና ቀጠሮን ጨምሮ

**የደህንነት ጊዜ፣** ከቤት ውስጥ ጥቃት፡ ጾታዊ ትንኮሳ ፡ማሳደድ ወይም የህዝብ ጤና ጉዳዮች*

### ከደሞዝ ጋር የህክምና እና የደህንነት (PSST) ጊዜ መጠን

| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 |
|---|---|---|---|
| **የአሰሪው መጠን** ሙሉ ጊዜ የሚስተካከለው ሰራተኞች (FTEs) አለም አቀፍ | **እስከ 49** FTEs | **50 – 249** FTEs | **250+** FTEs |
| **PSST የሚገኝበት** በሰአት የተሰራው | **1 ሰአት** በ 40 ሰአቶች | **1 ሰአት** በ 40 ሰአቶች | **1 ሰአት** በ 30 ሰአቶች |
| **ካለፈው የዞረ ጥቅም ላይ ያልዋለ PSST** በአመት | **40 ሰአቶች** | **56 ሰአቶች** | **72 ሰአቶች**** |

*የደህንነት ጊዜ የቤተሰብ አባልን ለመንከባከብ መጠቀም ይቻላል

**108 ሰአቶች ለደረጃ 3 ሰራተኞች ከክፍያ ጋር እረፍት ፖሊሲ (PTO)

## ፍትሃዊ የስራ እድል

የፍርድ እና የእስር ሪከርድ መጠቀምን ይገድባል

**የተከለከለ፣**

- የተፈረደባቸውን ወይም የእስር ሪከርድ ያላቸውን አመልካቾች የሚከለክሉ የስራ ማስታወቂያዎች
- የስራ ማመልከቻዎች ስለ ፍርድ ወይም የእስር ሪከርዶች ጥያቄ ያላቸው፣ አሰሪው አስቀድሞ ስለ ዝቅተኛ መመዘኛዎች አመልካቹን አጣርቶ ካልሆነ በስተቀር
- ስራ መከልከል (ወይም ሌላ የከፋ የስራ እርምጃ) የእስር ሪከርድን ብቻ መሰረት ያደረገ

**ከ 16 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት ቁጥጥር የሌለው የስራ ተዳርሶ፡ የእድገት ጉድለቶች ያለባቸው ሰዎች ወይም ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን የሚያካትቱ አንዳንድ ልዩነቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፣**

**አሰሪዎች እንዲህ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣**
አመልካቾች ለዝቅተኛ መስፈርቶች እስኪለዩ ድረስ የወንጀል ታሪክ ምርመራን ማዘግየት

የቀድሞ የወንጀል ታሪክን መሰረት በማድረግ ብቻ የከፋ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የአሰራር አግባብ መከተል፣

» የወንጀል ታሪክ ማረጋገጫ መረጃውን ለመግለጽ ወይም ለማስተካከል እድል መስጠት

» ቢያንስ ለሁለት የስራ ቀናት የስራ መደቡን ክፍት አድሮጎ መቆየት

» ግለሰቡን መቅጠር ስራውን እንደሚጎዳ ወይም የሰራተኛውን ስራ የመስራት ችሎታ ላይ ተጽእኖ ያለው ስለመሆኑ ህጋዊ የስራ ምክንያት ይኑር

## የደሞዝ ስርቆት

ከደሞዝ ስርቆት ጥበቃ ይሰጣል

አሰሪዎች  ሁሉንም የካሳ ክፍያዎች በመ ደበኛ የመክፈያ ቀን መክፈል እና ለሰራተኞች ስለ ስራቸው እና ክፍያው የጽሁፍ መረጃ ሊሰጧቸው ይገባል።

**የጽሁፍ መረጃ ማካተት ያለበት፣**

- የአሰሪው ስም እና የሚገኝበት መረጃ
- የሰራተኛው የክፍያ መጠን ፣ የትርፍ ሰአት ክፍያ ለማግኘት ብቁ መሆኑን፣ የክፍያው መሰረት (ሰአት፣ ሺፍት፣ ቀን፣ ሳምንት፣ ኮሚሽን)፣ መደበኛ የክፍያ ቀን
- የአሰሪው የጉርሻ ፖሊሲ
- በክፍያ ቀናቶች በንጥል የተያዘ የክፍያ መግለጫ

**የክፍያ መስፈርቶች ምሳሌዎች፣**

- ዝቅተኛ የደሞዝ ክፍያ
- የትርፍ ሰአት ክፍያ
- የእረፍት ሰአት ክፍያ
- ቃል የተገባለት መጠን ክፍያ
- ለሙሉ ቀን ስራ ክፍያ
- የጉርሻ ክፍያ
- የአገልግሎት ክፍያ (በደረሰኙ ወይም በምግብ ዝርዝሩ ውስጥ ደንበኛውን ለሚያገለግለው ሰራተኛ(ኞች) ተከፋይ የማይሆን ካልተገለጸ በስተቀር)
- የአሰሪውን ወጪዎች ተመላሽ አድርግ
- ሰራተኞችን በተሳሳተመንገድ መመደብ አይቻልም

## የተጓዥ ጥቅማጥቅሞች

20 ወይም ከዚያ በላይ ሰራተኞች ያሏቸው አሰሪዎች፣ በሳምንት በአማካይ አስር ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ለሚሰሩ ሰራተኞቻቸው፣ የትራንዚት  ወይም በቫን ተሰባስቦ መጓጓዣወጪዎችን ከሰራተኛው ግብር ከሚጣልበት ደሞዝ ላይ የፌደራል የግብር ህግ እስከሚፈቅደው ከፍተኛ መጠን ድረስ  እንዲያቀናንሱ ማስቻል አለባቸው። ይህን መስፈርት ለማሟላት፣ አሰሪዎች ከዚያ ይልቅ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ድጎማ የተደረገለት የትራንዚት የይለፍ ወረቀት ሊያቀርቡ ይችላሉ። አሰሪዎች ይህን ጥቅማጥቅም ከሰራተኛው የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በ60 የካላንደር ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው።

## ያነጋግሩን

**ሠራተኞች**
አቤቱታዎን OLS ጋር ያቅርቡ ወይም በፍርድ ቤት ክስ ይመስርቱ

**አሠሪዎች**
የመታዘዝ ድጋር እና/ወይም ስልጠና ያግኙ

**206-256-5297**
www.seattle.gov/laborstandards

810 THIRD AVE, SUITE 375
SEATTLE, WA 98104

LABORSTANDARDS@SEATTLE.GOV